# ኢ.ዴ.አ.ፓ - መድኅን
# UEDP - MEDHIN

Head Office ☐ Branch Office ☐ Support Group ☐


ቀን 18/06/00
Date

ቁጥር ኢ/መ 081/2000
Ref.

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>በፍቼ ምርጫ ጣቢያ ያጋጠሙ ችግሮችን ስለማሳወቅ፣</u>

በመጪው ሚያዚያ 2000 ዓ.ም በሚደረገው የአካባቢና ማሟያ ምርጫ ኢዴአፓ-መድህን ተሳትፎ እንደሚያደርግ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ፓርቲያችን ለቀበሌ ለወረዳ ለክልልና ለተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደሩ እጩ አባላትን አስመስግቧል። ይሁን እንጂ በሰሜን ሸዋ ዞን በፍቼ ምርጫ ጣቢያ በእጩ ተወዳዳሪነት እንዲመዘገቡ ያቀረብናቸው አርባ እጩዎችን "የፓርቲ አባልነት ውክልናችሁ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ አንመዘግብም" በመባላቸው ሳይመዘገቡ ቀርተዋል። በወቅቱ ችግሩን ለመፍታት ለቦርዱ በስልክ በተደጋጋሚ ባሳወቅነው መሠረት ችግሩ እንደተፈታና መመዝገብ የሚችሉ መሆኑ ቢገለፅልንም አስፈፃሚዎቹ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ጥረታችን ሳይሳካ ቀርቷል። ነገር ግን -

1ኛ. ማንኛውም ዜጋ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት በምርጫ ሕጉ የተጠቀሰውን መስፈርት አሟልተው የቀረቡ እጩዎች መሆናቸው እየታወቀ፣

2ኛ. ፓርቲያችን አባላቱን እጩ ሆነው እንዲወዳደሩ በምርጫ ጣቢያው የመደባቸው መሆኑን የሚገልፅ ሕጋዊ ደብዳቤ ማቅረቡ እየታወቀ፣

3ኛ. አንድን ፓርቲ ወክሎ እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ የግድ የፓርቲ አባል መሆን አለበት የሚል ሕግ እንደሌለ እየታወቀ ከእጩ ምዝገባ ስራ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌለው ምክንያት ሆን ተብሎ የተሰራ በመሆኑ፣

4ኛ. በማስረጃ የተደገፈ ቅሬታ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት እንዳይመዘገቡ መከልከላቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም አስፈፃሚዎቹ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

እነዚህ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከአድሎአዊ አሰራር በፀዳ መልኩ በገለልተኝነትና በእኩልነት ፓርቲዎችን እንዲያገለግሉ በምርጫ ህጉ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ አልተወጡም። ስለሆነም ቦርዱ ችግሩን በአስቸኳይ አጣርቶ ያለበቂ ምክንያት ያልተመዘገቡ እጩዎቻችን እንዲመዘገቡና ይህንን ተግባር የፈፀሙ የምርጫ አስፈፃሚዎች ወደፊትም በሚከናወነው የምርጫ ሂደት ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ላለመፈፀማቸው እምነት ያጣን በመሆኑ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ሙሴ ሰሙ
ዋና ፀሐፊ


Head Office ☎ 50 87 27 ✆ 50 87 30 ✉ 101458
Addis Ababa 50 87 28 E-mail:addisedepa@hotmail.com
Our Account No. Addis Ababa, Bank of Abyssinia Filwuha Branch A/C 145
Branch Office or Support Group in ______ Tel: ______ Fax: ______ P.O.Box: ______